# የመጨረሻው ሰይጣን
# መሽ አዳሪ

ከበልጅግ አሊ
ከአለፈው የቀጠለ

- እንደምን ከረሙ እማማ? ደህና ከረሙ?
- ደህና ነኝ። አንተን ስጠብቅ ከረምኩ። ይህንን ታሪክህን መጨረሻውን ለመስማት እየጓጓሁ እስከ አሁን ስጠብቅ ነበር። እንደው የሚያሳዝነው እንዲህ መደረጉ ነው ። እዛ እኛ ቤት በታች ያለውን የድባቤን ልጅ አታስታውስም። አካሉን በግርፋት አጉድለውት ስንት አመት ተሰቃየ። አሁንም ጭምር እንዳነከሰ ነው ያለው። ወያኔዎቹ ሲመጡ እሱ ነበር አንዱ ቀበሌዎችን ለማጋለጥ የሚራወጠው። የሰፈሩ ሰው ታዲያ ይህ ተግባር አይበጅም። እነዚህም ቢሆኑ ይብሳሉ እንጂ ከነዛ አይሻሉም። አይሆንም ቢለውም አልሰማም ብሎ ነበር። በኃላም ወያኔዎቹ የተጋለጡትን ፈትተው ጠላት አፈራ እንጂ የበጀም ነገር አላገኝም።ይባስ ብለው ቀበሌም የተመረጡት ተመልሰው የደርግ ካድሬዎቹ ሆኑ።
- አይ እማማ ከአንዳንዶቻችንስ የሞቱት ይሻላሉ። ስንት አይነት ስቃይ በላያችን ላይ አልፎል። አሁንም ቢሆን እንቅልፍ ይነሳናል። እኔም ስንት የማስታውሳቸው ነገሮች አለ መሰሎት ። አንዳንዴ አልፈን አልፈን እዛ የጨካኞች ግቢ ውስጥ አብረን የነበርን ስንገናኝ እንባችን ማቆሚያ የለውም። የሞቱትን እናስታውሳለን።አካላቸው የጎደለውን እናስታውሳለን። እያለቀስን እንስቃለን። እየሳቅን እናለቅሳለን። ለአንዴም ለሁሌም ግን የልጅነታችንን ጣፋጭ ዘመን በነዚህ አረመኔዎች ተወርሰን የመከራ ትዝታችንን ስናልም እንከርማልን። ብርድ ሲነሳ የአቄመው አካላታችን ሲቆጠቁጠን አዕምሮአችንን ይሰልበናል። ተደብቀን ስቅስቅ ብለን እናለቅሳለን። እርስ በርሳችን ስንገናኝ ብቻ ነው ነገራችንን ሳይሰለቸን የምንወያየው። ለሌሎቹማ ያለፈ አፈ ታሪክ ሆኑዋል።

- ለዚህም አደል ልጄ በደም የተሰራው ሃውልታችሁ አንድ ሆኖ ለዘላለም እንዲኖር ሁላችንም የምንፈልገው። በተለያየ ጊዜ በስማችሁ እኮ የተነሱ ሃሳዊ መሲሂዎችን ሕዝቡ አልቀበልም ያለው ለዚህ አደል። አሁንም ወደፊትም እንዲሁ ቢነሱ ማንም አይቀበላቸውም።የኢሕአፓነት ዋናው መለያነቱ ለሃቅ ለህዝብ መሰዋት ነው።እንደዛም እንደሆን በደማችሁ ተፅፎአል። ለጥቅም ለስልጣን መዋከብን የኢሕአፓነት ጠባይ ነው ብሎ የሚያምን ማንም የለም። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የቆየ ታሪክ እየደበዘዘ ይመጣል። አዳዲሱ በአሮጌው ይተካል።አዳዲስ አድርባዮች ብቅ ማለታቸው የማይቀር ነው።ቢሆንም ግን በታሪክ ውስጥ የክብር ቦታ ይዞ መገኘትን የመሰለ አኩሪ ተግባር የለም። ባለፈው እለቅሶ ላይ ሃዳስና ቆንጅት እንደተለመደው ክርክር አንስተው ነበር።ታዲያ ቆንጅት ለሃዳስ ለሃቅ ብሞት ይሻለኛል ብትላት ሃዳስ እንደተለመደው መልስ አታጣም አደል። ከኢሕአፓ በኃላ ለሃቅ የሚሞት አንቺ የመጀመሪያ ትሆኛለሽ ብላ አሳቀችን። እውነቷንም ነው ከዛ ዘመን በኃላ የበዛው ከሃጂ እንጂ የረባም ነገር ሳናይ እዚህ ደረስን።እስቲ ቀጥልልኝ ልጄ በአለፈው ካቆምክበት። ከሰቀሉበት ሲያወርዱህ ነበር የቆምከው።
- እሽ እማማ ከፈለጉ እቀጥላለሁ ።

ከተሰቀልኩበት አውርደው ከጣሉኝ በኃላ ሁለመናዬን ቢያመኝም ከተንጠለጠልኩበት በማረፌ ደስታ ተሰማኝ።ገራፊው ተነስ ብሎ ሲያንባርቅብኝ ጉልበቴ ቢከዳኝም ተነሳሁ። አዲስ መሄድ እንደሚለምድ ህጻን መንቀጥቀጥ ጀመርኩ። እግሬ የኔ ሆኖ አልታይህ አለኝ። ከመገረፊያው ቤት በራፍ ላይ ሌሎች የሚገረፉትን ስመለከት አዘንኩላቸው። እነርሱ ደግሞ እኔን እንደዚያ ሆኜ በማየታቸው ሳይደነግጡ የቀሩ አይመስለኝም። በአበጠ ፊቴ በቆሰለ እግሬ እየተውተረተርኩ ወደውጭ ወጣሁ። ታላቁን ጉዞ ተያያዝኩት ከተገረፍኩበት እስከማረፊያ ቤቱ ባልሳሳት 300-400 ሜትር ቢሆንም እርቀቱ ግን የወር ጉዞ ይመስላል።አብሮኝ እንዲያደርስኝ የተላከው ወታደር በዛ በአበጠው እግሬ እንደህፃን ልጅ ስውተረተር እያየ በፍጥነት እንዲሄድ ይጮህብኛል። አይቀርምና ስወድቅ ስነሳ እንደምንም ብዬ ጠዋት ጥያቼው ከመጣሁት ጋር ተደባለቅሁ።

ግማሾቹ ሲያዩኝ ደነገጡ ግማሾቹ ለነገው ዝግጅት እንዳደርግ ይጨቀጭቁኝ ገቡ።ግማሾቹ ግድግዳውን እርገጥበት ያበጠው ይጎድልልሃል ይሉኛል። ግማሾቹ ደግሞ ተነስና ቁምበት ይሉኛል። እኔ ግን ሁሉንም ትቼ አረፍ ለማለት ለመቀመጥ ብሞክር ስላልቻልኩ ወደቅሁ። ለትንሽ ግዜ እረፍት ተሰማኝ ውሃ ብጠይቅ እንደሌለ ተነገረኝ። ሁሉም ቦታ ያመኝ ጀመር። ሁለመናዬ ቁስል ሆኖ ተሰማኝ።እንደምንም ብዬ ለነገም ዝግጀት ባደርግ ብዬ እግሬን እግርግዳው ላይ መርገጥ ብሞክርም ስጋዬ

የኔ ስጋ መስሎ አልሰማህ አለኝ። ሙከራዬ ተስፋ እንደሌለው ገባኝ። አቅም አጣሁ። ድካም፣ርሃብ፣ጥማት፣ ተባብረው የነገውን ዝግጅቴን ተስፋ አስቆረጡኝ።

እንደገና ተመልሼ ወደቅሁ። ስቃይ በዛብኝ እንቅልፍ እንቢ አለኝ፣ሞቴን ተመኘሁ። አሁን ተሰቅለው ያሉትን ፣የሚገረፉትን አሰብኩ። ስገረፍ ያጎረሱኝ ኳስ ትዝ አለኝ። እንደገና ማጓጎጥ ጀመረኝ። ምንም ስለሌለ ምንም የሚወጣ ነገር የለም። ቤቱ እየሞላ መጣ። ከነበረው በላይ ተጠቀጠቀ። እግሬን ማለት፣ መጮህ ተጀመረ። የተገረፈው በዛ። ለመገረፍ የሚጠብቀው በስቃይ ላይ የሚገኙትን በመመልከት ጭንቀት ዋጣቸው። ነገ ምን እንደሚጠብቃቸው ስላወቁት ከተገረፉት በላይ ሃሳብ ዋጣቸው። ከተገረፍነው ውስጥ መፈክር የሚሰማም አለ። እናቸንፋለን ፣ ድል ለኢሕአፓ፣ ሌላም ፣ ሌላም። በደከመ ድምጽ መፈክር ማሰማት። ምሽት ላይ በተራ ወደ ሽንት ቤት እንድንወጣ ታዘዝን እኛ የተገረፍነው መሄድ ስላልቻልን ውሃ እንዲያመጡልን ጠየቅን። ወጥተው የተመለሱት ውሃ ይዘውልን መጡ እሷን ተቃመስን። ሌሊት ላይ በሩ ተንኳኩቶ ተከፈተ ካለነው መካከል አንዳንዶቹ ተጠሩ ብዙዎቹ ከተገረፍነው ማህል ነበሩ። ሁሉም አዘን ዋጠው።በዛ ሰአት ተጠርተው የሚወጡ እንደማይመለሱ የታወቀ ነበር። በሩ ሲከፈት ከቤቱ የሚወጣው እንፋሎት ቤቱ ምን ያህል እንደታፈነ ያስታውቅ ነበር።ግማሾቹ መፈክር አሰሙ። ግማሾቹ መዘመር ጀመሩ። ሁሉም ከወጡ በኋላ ቤቱ ተመልሶ ተዘጋ። የሁላችንንም ሃሳብ ከነርሱ ጋር አብሮ ነጎደ። እንደተጮኸም ነጋ።

*አይነጋም የለምና ቀኑ ነጋ*
*የስቃይ ቀን ሊጀመር*
*ጣርና ሞት ሊፈራረቅ*

በመነጋታው እንደተለመደው ስሜ በመጀመሪያ ተጠራ። እስከአሁን በሚገርመኝ ሁኔታ ከየት እንደመጣ በማላውቀው ሁኔታ ተፈንጥሬ ተነሳሁ። አሁን የማስታውሰው ቢኖር ሌሊት ተጠርተው የተወሰዱና የተገደሉትን ሳስብ እኔ እንዴት ለፋሽሽቶች ግርፋት ፍርሃት ይሰማኛል ብዬ ሳወጣ ሳወርድ ነበር ያደርኩት። ያ የረዘመብኝን መንገድ በቆራጥነት ወጣሁት። ወደ ቢሮ ተወስጄ የምናገረው እንዳለኝ ተጠየቅሁ። ምንም እንደሌለኝ ስናገር በቡጢ ያዙኝ። ወደ መግረፊያው ክፍል ተወስጄ በፍጥነት ለወፌ ተዘቀዘቅሁ። ሰውነቴ በመድከሙም ይሁን በመጠንከሬ ግርፉ ግርፍ አልመስልህ አለኝ። ምንም ለውጥ ስላላዩብኝ ይመስለኛል በስለት ውስጥ እግሬን ቆረጡት።ሞላ ተረከዜን አነሱት። በጣም ተሰማኝ። ጓጎጥኩ፣ ተንፈራገጥኩ፣ ሁለመናዬ ስለታሰረ ምንም መንቀሳቀስ አልቻልኩም ዱላው ቀጠለ። ካዛ ምን እንደሆንኩ አላውቅም። የተነሳሁት ውሃ ሲያፈሱብኝ ነው ። ሌሎች እስረኞች ተጠርተው እግሬን በጨርቅ ሸፈኑልኝ። ደሜን ለማቆም ሞከሩ ተሸክመውኝ እስር ቤት ወስደው ጣሉኝ። አንዴ ስነቃ አንዴ ፣ አንዴ ነፍሴን ስስት ቀናት ያልፉ ጀመር። ከእግሬ አልፎ ወደ ጨርቁ የፈሰሰው ደም መሽተት ጀመር። ስጋዬ እላዬ ላይ ተላ። ደከምኩ። ሰውነቴ ዛለ። አንድ ቀን እስር ቤቱ ለሌሎች እስረኞች ሰለተፈለገ በትልቅ መኪና ተጭኜ ወደ ከርቸሌ መጥቼ በመሸ አዳሪነት ተጣልኩ።

- ምንድነው መሸ አዳሪ ልጄ?
- መሸ አዳሪማ እማማ „ወራንት" ያልተቆረጠለት እስረኛ ነዋ። ቀለብ ያልተሰፈረለት። አንድ ቀን ሊወሰድ በባለስልጣን በአደራ የተቀመጠ ፍጡር ማለት ነው።
- ስንት ጉድ አለ ልጄ በየቤቱ።
- አይ እማማ ስንት ሰቃይ አየን። በሃገራችን እንደ ጠላት ይህ ሁሉ መከራ ደረሰብን። ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ሆነን በበሽታ አካለ ጎደሎ ሆነን እንኖራለን ። እንሰቃያለን ፣ እናለቅሳለን።
- አዬ ልጄ ዘመኑ እኮ የከይሲ የከሃዲ ዘመን ነው። ያ ከእናንተ ጋር የነበረው አሁን ደግሞ ከወያኔዎች ጋር ተመልሶ የመጣ ታስታውሰዋለህ። የጡረተኛው የአስር አለቃ ልጅ።
- አዎ አስታውሰዋለሁ እንጂ።
- ታዲያ እሱ ያኔ ከእናንተ ጋር በአላማ ተለያይቻለሁ በማለት ለደርግ አድሮ ነበር። ከቀይ ሽብር አካባቢ የመንግስት ካድሬ ሆኛለሁ ብሎ አጭር አውቶማቲክ ጠበንጃ ይዞ በየጓደኞቹ ቤት እየሄደ ሲያሲዝ ፣ የጓደኞቹን ወላጆችን ሲሳደብ ነበር ። አባቱም ይህንን ሲያዩ ልጄ አደለም ብለው ካዱት። የሰፈሩም ሰው እረገመው። ከዛም የሰፈሩ ሰው አይንህ ላፈር ሲለውና፣ደርግም ተጠቅሞ ሲጥለው ግብርና ሚኒስቴር ተቀጥሮ ወደ ሰሜን ሄዶ ነበር። በኋላም ወያኔ ወሰደችው ተብሎ ተወርቶ በዛው ይጠፉል ሲባል ከወያኔ ጋር አብሮ እንደለመደው አውቶማቲክ ጠበንጃውን ይዞ ተመለሰ። ታዲያ አንድ ቀን ሃዳስ እንደለመደችው ለቅሶ ላይ ለሚቀጥለውም መንግስት አንድ አውቶማቲክ ገዝቶ አስቀምጦአል ብላ ስታስቀን ነበር ። ልጄ አንዳንድ ሰው እኮ ከሃጂነቱን ይደጋግመዋል።
- ልክ ነው እማማ ከሀጂነት ባህል የሆነላቸው አሉ።

**ይቀጥላል።**